ኢሰመጉ

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

ኢሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!

EHRCO Stands for Democracy, the Rule of Law and the Respect of Human Rights.

## አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ

## በህይወት የመኖርና የአካል ደህንነት መብት ይከበር!

ነሀሴ 7 2012 ዓ.ም

ነሀሴ 3 ቀን 2012 ዓ.ም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ ጉታራ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በስብሰባ ላይ ሳሉ የዞኑን ዋና አስተዳዳሪን ጨምሮ ሌሎች የዞኑ ባለስልጣናትና ግለሰቦች ‹‹ሀገር ለማፍረስ ከሚንቀሳቀሱ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር እና ሕገ-ወጥ አደረጃጀቶችን ፈጥረው ግጭት ሊቀሰቅሱ ነበር›› በማለት በሕግ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ማድረጉን መንግስት መግለጹ ይታወሳል፡፡ ይህን ክስተት ተከትሎ በተለይም በሶዶ፣ በቦዲቲ እና በአረካ ከተሞች ላይ ተቃውሟቸውን ለማሰማት አደባባይ በወጡ ዜጎች ላይ በሥፍራው የነበረው የክልል እና የፌደራል የጸጥታ ኃይል የኃይል እርምጃ በመውሰዳቸው የበርካታ ንጹኃን ነፍስ ተቀጥፏል እንዲሁም አካል ጎድሏል፡፡ በመንግስት የፀጥታ ሀይሎች የተፈፀመው ግድያም ሆነ አካል ማጉደል በፍፁም ተቀባይነት የሌለው ነው ብሎ ኢሰመጉ ያምናል፡፡

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት እንዳለው በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ ያጸደቀቻቸው እና የአገሪቱ የሕግ አካል የሆኑ ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሥምምነቶችም ፈራሚ አገራት ይህንኑ መብት የማክበር፣ የማስከበር፣ የመጠበቅ እና የማስተዋወቅ ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋሉ፡፡ ነገር ግን መንግሥት ራሱ ፈርሞ ግዴታ የገባባቸውን የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች በሚጥስ መልኩ በንጹኃን ዜጎች ላይ በወሰደው እርምጃ ሞትና የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

መንግስትና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ከአሁን ቀደም የክልልነትና የአደረጃጀት ጥያቄዎችን ተከትሎ ከተፈጠሩት ተመሳሳይ ኹነቶች ትምህርት በመውሰድ በሕጋዊ መንገድ መልስ ለሚያገኝ ጥያቄ በሰው ሕይወት እና አካል እንዲሁም በሕዝብም ሆነ በመንግሥት ንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ሊያስቀር በሚችል መልኩ ጥያቄዎችን መፍታት ተገቢ ሆኖ ሳለ፣ ተመሳሳይ ጥፋት በሚያስከትል መንገድ ላይ በድጋሚ መገኘቱ፣ በሰብዓዊ መብቶች መከበርና መጠበቅ ላይ በርካቶች ጥለውት የነበረውን ተስፋ የሚያጨልም እንዳይሆን ጥንቃቄ እንዲደረግ ኢሰመጉ በጥብቅ ያሳስባል፡፡

በመሆኑም የፌደራልም ሆነ የክልሉ መንግሥት አሁንም ተጨማሪ ሰብዓዊ ቀውሶች እና ጥፋቶች ከመድረሱ በፊት ለአደረጃጀት (የክልል እንሁን) ጥያቄው አፋጣኝ አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ መፍትሔ በመስጠት ለችግሩ እልባት እንዲሰጡ

ኢሰመጉ ያሳስባል፡፡ መንግሥት ከሰሞኑ ለተፈፀመው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ኃላፊነት ሊወስዱ የሚገባቸውን ሰዎች በአፋጣኝ በምርመራ በመለየት ህጋዊና ተገቢ እርምጃ እንዲወስድ እና ለተጎጂዎችም ተገቢውን የሞራል እና የገንዘብ ካሳ እንዲከፍል ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

መንግሥት አሁን ያለውን ተጨባጭ የጸጥታ ሁኔታ ከዞኑ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ምሁራን፣ አመራሮች፣ ነዋሪዎች እና ወጣቶች ጋር በመወያየት በአፋጣኝ እንዲያስተካክልና የሚመለከታቸው የመንግሥት እና የሲቪክ ማኅበራት ድርጅቶች በቦታው ተገኝተው የደረሰውን ጥፋት እንዲመረምሩ የሚያስችል ሁኔታ እንዲያመቻች ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም መንግሥት በወንጀል ተጠርጥረው በሕግ ጥላ ሥር የሚገኙ ዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች እንዲያከብር፣ ከቤተሰቦቻቸው እና ከጠበቆቻቸው ጋር የመገናኘት መብታቸውን እንዲያረጋግጥ እና ለኮሮና ቫይረስ አጋላጭ ባልሆነ አያያዝ ሥር ሆነው ሰብዓዊ ክብራቸው እና ሕጋዊ የዋስትና መብታቸው ሳይሸራረፍ እንዲያከብር እና እንዲያስከብርላቸው ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

በመጨረሻም ኢሰመጉ ለመላው ኢትዮጵያዊያን አሁን ሀገራችን የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በከፍተኛ ኃላፊነት እና ጥንቃቄ ነገሮችን እንዲከታተሉ፣ የእርማት አስተያየቶችን እንዲያቀርቡ፣ የማንኛውንም ግለሰብም ሆነ ቡድን ክብር እና ማንነት ብሎም የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ ከሚጥሉ አስተያየቶች እና ንግግሮች እንዲቆጠቡ ለማሳሰብ ይወዳል፡፡

ነሀሴ 7 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ፡፡

**ሁሉም መብቶች ለሁሉም!!**

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም አቀፍ ጸረ-ሥቃይ ድርጅት (OMCT) አባል፣ የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ጥበቃ ኅብረት (Defend Defenders) መሥራች አባል ነው፡፡